ዓለምለኸ ማሕበር ዴሞክራሲያዊያን ተጋሩ

አለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማህበር.
International Tigrean Democratic Association

itda2005@yahoo.com


# አፈናንና ሽብርን ለማጠናከር የሚደረግ ምርጫ

በዓለማችን በተለያዩ አገሮች ምርጫዎች በየጊዜው እንደሚካሄዱ ይታወቃል። ከማንኛውም ጊዜ በበለጠ ባለንበት የግሎባላይዜሽን (ሉላዊነት) ዘመን፣ ዘመናዊ የመገናኛ ብዙሀን (ሬዲዮ፣ ቴሌቭዥን፣ ኢንተርንት፣ ……ወዘተ) የተስፋፉበት እንደመሆኑ፣ በየጊዜው በየአገሩ የሚደረጉ ምርጫዎችና የምርጫ ውጤቶችን መከታተል አዳጋች አይደለም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በገነቡ አገሮች፣ የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ስለሚከበሩና፣ የሕግ የበላይነትም ስለሚረጋገጥ ፓርቲዎች በነፃ ተወዳድረው አሸናፊው ነፃና ፍትሓዊ በሆነ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ይለያል። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለሙያዎች በሚያደርጉት ጥናትና ምርምር የምርጫ ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ለመተንበይ ቢቻልም፣ በቅድሚያ ውጤቱን በእርግጠኝነት ማወቅ ግን አይቻልም። በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ውስጥ ማጭበረበር ብሎ ነገር የማይኖር ቢሆንም፣ በምርጫው አንዳንድ ቴክኒካዊ ችግሮች ቢፈጠሩና፣ በዚህ ምክንያትም የምርጫ ውጤት አወዛጋቢ ሆኖ ቢገኝ፣ ችግሩ በሕጋዊና የተሟላ ግልጽነት በተላበሰ አሠራር ይፈታል። ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምርጫ  የህዝብ ሉዓላዊነት የሚገለፅበት፣ የሚከበርበት፣ የሚተገበርበትና ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ የሚተላለፍበት በመሆኑ እስካሁን የሰው ልጅ የደረሰበት ሥልጡን ህብረተ-ሰባዊ ሥርዓት ነው ሊባል ይችላል።

በአንፃሩ በኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚደረግ ምርጫ፣ ቁልፍ የሆኑ ተቋማት በገዢው ፀረ-ዴሞክራሲ ፓርቲ ወይም አገዛዝ ቁጥጥር ሥር ስለሚሆኑ፣ ነፃና ፍትሓዊ ምርጫ አይካሄድም። የምርጫ ዝግጅቱ ሂደት የምርጫውን ውጤት ሊወስን በሚያስችል መንገድ ተቀይሶ ስለሚከናወን፣ አሸናፊ ማን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ምንም ዓይነት ጥናትና ምርምር አይጠይቅም። ስለሆነም የምርጫው አሸናፊ ምርጫው ከመደረጉ በፊት አገዛዙ (ልክ በቅርቡ በሩስያ እንደተደረገው ምርጫ) እንደሚሆን ካለ ጥናትና ምርምር በእርግጠኝነት የሚታወቅበት ሂደት ነው። በዚህ መልክ የተጭበረበረውን ምርጫ ተከትሎ ተቃውሞ ከተነሳም፣ ፀረ-ዴሞክራሲያዊው አገዛዝ የተቃዋሚው ፓርቲ መሪዎችና ደጋፊዎችን በማሰርና እንዲሁም በመግደል ተቃውሞውን ለማዳከም ይሞክራል። በሌላ በኩል፣ ምርጫ ቢጭበረበርም፣ እንደ የጦር ኃይል፣ ፖሊስና የፍርድ ሥርዓት የመሳሰሉ ቁልፍ

ተቋማት በቀጥታ በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር ካልሆኑና የተወሰነ ተቋማዊ ነፃነት ካላቸው፣ ተቃዋሚ ኃይሉም የተጠናከረ ከሆነ፣ በህዝብ እምቢተኝነትና አመፅ የተጭበረበረው ምርጫ ሊሻር እንደሚችልና የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደትም እንደሚቀጥል የዩክሬይን የብርቱካን አብዮት (Orange Revolution) እንደ ትልቅ አብነት ሊጠቀስ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሥልጣን የያዘ መሪና ፓርቲ በአገሪቱ ያሉት ተቋማት ካለመጠናከር የተነሳ ምርጫውን አጭበርብሮ በአገሪቱ የደም መፋሰስ እልቂት ሊያስከትል እንደሚችል ከዚያም በውጭ ኃይሎች ጫና ስምምነትና መረጋጋት እንደሚፈጠር የቅርቡ የኬኒያ ምርጫ አሳይቷል።

ምርጫን በሚመለከት የሚስተዋለው የተለያየ ሂደትና ውጤት፣ ማለትም ባንድ በኩል ፍትሓዊነትና ዴሞክራሲያዊነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሽፍጥ፣ ማጭበርበርና ይህንንም ተከትሎ የሚደርሰው ህብረተ-ሰባዊ ቀውስ በተለይም የቀዝቃዛው ጦርነት (Cold war) ካከተመ በኋላ በየጊዜው የሚታይ ክስተት ሆኗል። የሶሻሊስትና የኮምኒስት ሥርዓት ገንብተናል ይሉ በነበሩ አገሮች ሥርዓቱ ከፈረሰ በኋላ፣ ቀዝቃዛው ጦርነት በማክተሙ፣ በአለማችን በተለያዩ መአዝናት የዴሞክራሲ ነፋስ እየነፈሰ ነው። በዓለም ታሪክ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በብዛት የዴሞክራሲ ሥርዓት የመገንባት ሂደት እየታየ ነው። በአንድ የሶሻሊስት ወይም የኮሚኒስት ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ ሥር የነበሩ እንደ ፖላንድ፣ ቼክ፣ ሩመኒያ፣ ሀንጋሪ፣ የባልቲክ አገሮች፣........ወዘተ. ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብቷል። በነዚህ አገሮች ነፃና ፍትሓዊ የሆነ ምርጫ በየጊዜው ተካሂዷል። በብዙ የሶስተኛ ዓለም አገሮችም ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መጀመሩ የታወቀ ነው። በአፍሪቃም እንደ ቤኒን፣ ጋና፣ ዛምቢያ፣ ደቡብ አፍሪቃ ......ወዘተ በመሳሰሉ አገሮች የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መካሄዱ፣ የዴሞክራሲ ጮራ በክፍለ ዓለማችን እየፈነጠቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በአፍሪቃም ሆነ በሌሎች አገሮች የተካሄደው ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያመራው ለውጥ ባብዛኛው ያለ ደም መፋሰስ የተካሄደ ነው። በቀድሞው የምሥራቅ ኤውሮጳ ሶሻሊስት አገሮች የቀድሞውን ገዢ ፓርቲን ጨምሮ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪል ማህበራትን ያሳተፈ የሽግግር መድረክ ተነድፎ ውጤታማ ሆኗል። በአፍሪቃም ለምሳሌ በበኒን ሁሉንም የህብረተ-ሰብ ክፍል ያሳተፈ ብሄራዊ ጉባኤ (National conference) ተካሂዶ ነበር ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር የተደረገው። ይህ ዓይነት የሽግግር ለውጥ የሁሉንም የህብረተ-ሰብ ክፍሎች ፍላጎት ያካተተ እንደመሆኑ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ የሆኑትን ተቋማት በድርድርና በስምምነት ነበር የተገነቡት። ምርጫም አስተማማኝ፡ ነፃና ፍትሓዊ የሆነው ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ከተገነቡና ከዚያም ትልቁ ተቋም ሕገ-መንግሥት በሁሉም ተሳታፊነትና ስምምነት ከተቀረፀና ከፀደቀ በኋላ ነው።

በአገራችን የተካሄደው የሥልጣን ሽግግር ግን ከብዙ አገሮች የተለየ ነው። አንድ አምባገነናዊ አገዛዝ በሌላ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው የተተካው። የደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ የተተካው ህውሓት በሚቆጣጠረው የኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ነው። ደርግን በጠመንጃ አሸንፎ የተካው የህወሓት አመራር ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያልታገለ ፍጹም ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነ ቡድን ነው። ይህ ቡድን ከተማሪው እንቅስቃሴ ያገኘውን ጥሬ የግራ ርእዮት ሰንቆ ያደገው በትግራይ በረሀ ነው። ይህ ቡድን አንዴ የትግራይን ሪፑብሊክ እመሰርታለሁ ከዛም ተሳስቻለሁ፣ አንዴ የማኦ

ዜ ዱንግ ተከታይ ነኝ እንደገና አይደለሁም እያለ ሲባዝን ቆይቶ፣ በመጨረሻ ከጳጳሱ (ከማርክስ) የበለጠ ሊቅ ነኝ ብሎ የኢንዱስትሪ ወዛደር በሌለበት ድሀ የትግራይ ህብረተ-ሰብ የወዛደሩን አምባገነንነት (Dictatorship of the Proletariat) እመሰርታለሁ ብሎ ህዝቡ በረሀብ እንደቅጠል በሚረግፍበት በ1985 ዓ. ም.ፈ ማሌሊት የሚባል ፓርቲ መስርቶ የቀለጠ ድግስ የደገሰ ፀረ-ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛ ቡድንም ነው። ድርጅታዊ መዋቅሩና አሰራሩ ስታሊናዊ ማእከላዊነትን የተከተለ እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ አወቃቀርና አሰራር ለድርጅቱ አባላት ቅንጣት ያህል ነፃነትና መብት የማይሰጥ ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ነው። በዚህ አሰራር የትግራይ ህዝብም በቡድኑ ርእዮትና እምነት እንዲደራጅ በኃይል ተገዷል። ከአመራሩ ርእዮት ፖሊሲና ትእዛዝ የወጡ ብቻ ሳይሆን ጥያቄም ያቀረቡ ብዙ የድርጅቱና የህብረተ-ሰቡ አባላት ታስረዋል፣ ተገድሏል።

ስለዚህ በኢትዮጵያ የአገዛዝ ለውጥ የተካሄደው እስከ 1989 ዓ.ም.ፈ ድረስ የአልባኒያው ኤንቨር ሆዣ ተከታይ ነኝ ሲል በነበረው፣ ፀረ-ዴሞክራሲ ብቻ ሳይሆን አገሪቱን ካለ ባህር በር ባስቀረው፣ ምርኮኞቹን ሰብስቦ ኢህአዴግ ነኝ ባለው የህወሓት ከሃዲ ቡድን ስለሆነ፣ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት (Democratization process) አልተካሄደም። በንድፈ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም በሌሎች፣ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ አገሮች ጭምር፣ የታየው ተቃዋሚ ኃይሎችንና ሌሎች የህብረተ-ሰብ ክፍሎችን ያሳተፈ የነፃ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ በአገራችን አልተደረገም። የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ በመቀየሩ ግን ህወሓት/ኢህአዴግ የዴሞክራሲ የውሸት ካባ ማጥለቅ ስለነበረበት የፕሬስ ነፃነት ፈቅጃለሁ ማለቱ ይታወሳል። ቢሆንም የኤሌክትሮኒክ ሚዲያውን (ራዲዮና ቴሌቪዥን) ብቻውን በመቆጣጠር፣ የፅሑፍና የጋዜጣ የፕሬስ መብት ለዓለም አቀፍ ህብረተ-ሰብ እንደናሙና ለማሳያ በአዲስ አበባ የተገደበ እንጂ በአገሪቱ እንዳይስፋፉ የተከለከለ ነበር። ይህ የተገደበ የፕሬስ መብት የፈቀደበት ምክንያትም ሌሎች ተቋማትን ለመቆጣጠር፣ (ለምሳሌ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ካድሬዎቹን በለብለብ እያሰለጠነ የፍርድ ሥርዓቱን እስከሚቆጣጠር) ጊዜ ለመግዛት የተጠቀመበት ታክቲክ ነው። በኋላ እንደታየውም ይህ የተገደበ የፕሬስ መብት ጋዜጠኞችን በማሰር አዳክሞ፣ በአሁኑ ጊዜ አጥፍቶታል ለማለት ይቻላል።

የመለስ ቡድን ተቋማቱን በቁጥጥሩ ሥር ውስጥ ካስገባና የሥልጣን ኮረቻውን ካደላደለ በኋላ፣ እንደሌላው አምባገነን አገዛዙን የዴሞክራሲ ሽፋን ለመስጠት በዛውም የውጭ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍና እርዳታ ለማግኘት “ምርጫ” አካሂደዋል። በአገዛዙ የተካሄዱት ምርጫዎች ነፃና ፍትሓዊ እንዳልነበሩ ከኢትዮጵያ ህዝብ የተሰወረ ስላልሆነ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ አስፈላጊ አይሆንም።

በእርግጥ በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከተካሄዱት ምርጫዎች ምርጫ 97 ልዩና ታሪካዊ እንደሆነ አይካድም። ምርጫ 97 ኢህአዴግ ለተቃዋሚዎች የተወሰነ /የተገደበ/ የፖለቲካ ቦታ (Political space) በመስጠቱ በከፊል ውድድር የታየበት (semi-competitive) ምርጫ ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት ኢህአዴግ ምርጫውን አጭበርብሮ እንደሚያሸንፍ (በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ) እርግጠኛ ስለነበረና በዚህም ለሥልጣኑ አደጋ እንደማይከሰት በመተማመን ነበር። ሌላው ምክንያት ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች እንዳሉት እንዲሁም ማህበራችን በምርጫው ጊዜ ባወጣው

መግለጫ እንደጠቀሰው አቶ መለስ በጊዜው ያለአገባብ በማጭበርበር አግኝቶት የነበረውን ዓለም አቀፍ እውቅና ለመጠበቅና በምርጫውም የበለጠ "ዴሞክራሲያዊ መሪ" እንዲባልም በነበረው ምኞት ነው።

በምርጫ 97 ተቃዋሚ ኃይሉ ያገኘውን በከፊል የመወዳደር መብት ተጠቅሞ ህዝቡን ለምርጫ ቀስቅሷል። የኢትዮጵያ ህዝብም (በስታሊናዊ መዋቅር ከታሰረው የትግራይ ህዝብ በስተቀር) ያገኘውን የመምረጥ ዕድል ተጠቅሞ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ብቁ መሆኑን ያስመሰከረበት ታሪካዊ ምርጫ ነው። ቢሆንም ምርጫው በህወሓት/ኢህአዴግ ከተጭበረበረ በኋላ ህዝቡ ድምጼ ይከበር ብሎ ለአመፅ ቢነሳም፣ ተቃዋሚው ኃይሉ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ ባህሪንና የመሪዎቹን መሠሪነት ጠንቅቆ ባለማወቅ፣ አገዛዙ ምርጫውን እንደሚያጭበረብር እየታወቀ የህዝቡን ዓመፅ የመምራት ድርጅታዊ ዝግጅት አለማድረጉና ይባስ ብሎም በውስጡ መከፋፈልና መካካድ በመከሰቱ ታሪካዊው ምርጫ ግቡን ሳይመታ ቀርቷል። ህዝቡን የከዳው የተቃዋሚ ኃይል ለህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች እጁን ሲሰጥ ያልከዳው ደግሞ ወህኒ ወርዷል። መሪ ድርጅት ያጣው ህዝብም የህወሓት/ኢህአዴግ እስራትና ግድያ ወርዶበታል። በዚህ ተግባሩም ህወሓት/ኢህአዴግ የጉዳዩ ባለቤት በሆነው በኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ህብረተ-ሰብም አምባገነናዊ አገዛዝ መሆኑ ተጋልጧል።

አምባገነናዊው የመለስ ቡድን ከምርጫ 97 ብዙ "ትምህርት" መቅሰሙ አከራካሪ አይደለም። በምርጫው የታየውን የህዝቡን የለውጥ ፍላጎትና ዓመፅ እንዳይደገም መጠነ ሰፊ እስራትና ግድያ አካሂዷል። ለአገዛዙ የዴሞክራሲያዊነት ሽፋን እንዲያገለግል ፈቅዶት የነበረው የተገደበ የፕሬስ ነፃነትም ጭራሹኑ አጥፍቶታል። በተጨማሪም ከምርጫ 97 በኋላ ለወደፊቱ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥያቄ እንዳይነሳ በዩኒቨርሲቲዎችና በሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎችና አስተማሪዎችን በግዴታ ምልመላ (Forced Recruitment) የህወሓት/ኢህአዴግ አባላት እንዲሆኑ አድርጓል፣ እያደረገም ነው። ስለሆነም ባሁኑ ሰዓት የአገራችን ዩኒቨርሲቲዎች፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የማይተማመኑበት፤ ተማሪዎች አስተማሪዎቻቸውን የማያምኑበትና የሚፈሩበት፤ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን የሚፈሩበት፣ በነፃ የማሰብና የመተቸት (Critical Thinking)፣ በነፃ የመመራመር መብት የሌላቸው፣ የዴሞክራሲ ባህል እንዳይዳብር የተደረገባቸው ተቋማት ሆነዋል። ይህንን የአካዳሚ ነፃነት እጦት በሚመለከት በቅርቡ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፕሮፌሰር የነበሩት ፕሮፊሰር ዓቢ ጋይል ሳሊስበሪ የፃፉት ፅሑፍ (ፅሑፉን ከፃፉ በኋላ ከሥራ ተባረዋል) መመልከቱ አንድ አብነት ነው።

ህወሓት/ኢህአዴግ ከምርጫ 97 በኋላ የአገዛዙን ዕድሜ የሚያራዝመው ባንድ በኩል የኢትዮጵያ ህዝብን ረግጦ በመግዛት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የውጭ ኃይሎች ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን ነው። ስታሊናዊ መዋቅሩን በበለጠ አጠናክሮ የኢትዮጵያን ህዝብ አሸብሮና አፍኖ ለመግዛት በቅርቡ የማሟያና የአከባቢ "ምርጫ" ያካሂዳል። የማሟያ "ምርጫው" በግንቦት 97 ምርጫ ተቃዋሚ ኃይሉ በተለይም ቅንጅት ያሸነፈውን ለመተካት ነው። በአዲስ አበባ ብቻ ቅንጅት ለፓርላማ ተወዳድሮ ባሸነፈባቸው 14 የምርጫ ጣቢያዎች እንደገና "ምርጫ" ይካሄዳል። ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤትም ቅንጅት ያሸነፈውን 137 የምክር ቤት መቀመጫ ለመተካት "ምርጫ"

ይካሄዳል። በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው ማለትም የቀበሌና የወረዳ “ምርጫ” ህወሓት/ኢህአዴግ ከ4 ሚሊዮን በላይ እጩ ተወዳዳሪዎች ማቅረቡ በይፋ እየገለፀ ነው። የሪፖርተር ጋዜጣ መጋቢት 5 ቀን 2008 ዓ. ም.ፈ. በዘገበው መሠረት፣ በአዲስ አበባ ብቻ ህወሓት/ኢህአዴግ ለአከባቢ ምርጫ 2070 እጩ ተወዳዳሪዎች ሲያቀርብ በግልና በሌሎች ፓርቲዎች ለውድድር የቀረቡት ግን 90 ብቻ ናቸው።

በዚሁ የማሟያና የአካባቢ “ምርጫ” ህወሓት/ኢህአዴግ፣ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ስለሆነ ብቻውን ተወዳድሮ “የሚያሸንፍበት” ነው። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ለሥርዓት ለውጥ የሚታገሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ በህወሓት/ኢህአዴግ ዱላ ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው እየተናከሱ፣ እየተናቆሩ፣ እየተከፋፈሉ የተዳከሙበት ጊዜ ነው። በኢትዮጵያ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው በተለይም በፓርላማ የተወሰነ መቀመጫ የተቸረው፣ የህወሓት/ኢህአዴግ አገልጋይ የሆነ፣ የሚሰጠውን ትእዛዝ እየተቀበለ የሚኖር፣ ለኢትዮጵያ ህዝብ ስቃይና መከራ ደንታ የሌለው ለሆድና ለሥልጣን ያደረ ነው። ስለሆነም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና እንዲሁም ለነፃና ፍትሓዊ ምርጫ ወሳኝ የሆነውን የተቋማት ነፃነትን ጥያቄ (አምባገነናዊው የመለስ ቡድን እንደማይቀበለው የታወቀ ቢሆንም) አይጠይቅም። “ተቃዋሚ” የሚለውን ቅፅል ስለለጠፈ ብቻ የሚያቀርበው ጥያቄና አቤቱታ አሳዛኝና አስቂኝ ነው። ለምሳሌ በአሁኑ “ምርጫ” ምድረ “ተቃዋሚ” በዋናነት የሚያቀርበው ጥያቄ አምባገነናዊው የመለስ ቡድን የፈለገውን የቅስቀሳ ሰዓት ቢፈቀድለት ምንም ለውጥ የማያመጣውን የአየር ሰዓት ድልድል ጥያቄ ነው። ቢሆንም ይህ ጥያቄ በኢህአዴግ ተቀባይነት አላገኘም ብቻ ሳይሆን አፈናውን እያጠናከረ በመሄዱ የተወሰነ “ተቃዋሚ” ክፍል ከምርጫው ራሱን እንዳገለለ እየገለጸ ነው።

አስቀድመን እንደገለፅነው፣ ህወሓት/ኢህአዴግ በአገሪቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ያቀረበው የአስተዳደር እርከኑን ከታች ጀምሮ ለመቆጣጠርና በከፋ መልኩ ስታሊናዊ መዋቅሩን ለማጠናከር ነው። በደርግ ዘመን እንደነበረው የቀበሌና የአብዮት ጥበቃ አስተዳደር፣ ከዚህ ምርጫ በኋላ በየቀበሌው፣ በየወረዳው “የሚመረጡት” የህወሓት/ኢህአዴግ ካድሬዎች በአገዛዙ የማእከላዊነት አሰራርና አወቃቀር የአምባገነኑን ገዢ ቀጥታ ትእዛዝ ተቀባዮችና አስፈፃሚዎች ይሆናሉ። የመለስ አምባገነናዊ ቡድን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉትን ተቃዋሚዎች ለማፈንና እንዲሁም ምንም ዓይነት ህዝባዊ እንቅስቃሴና ተቃውሞ እንዳይነሳ የህብረተሰቡን ህይወት ለመቆጣጠር የስለላና የአፈና መዋቅሩን ለማጠናከር የሚያደርገው “ምርጫ” ነው።

የዚህ ምርጫ ዋናው ግብ ህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዙን ለብዙ ዓመታት ለማቆየት መሆኑ አያጠራጥርም። ካሁኑ መፍትሔ ካልተፈለገ አምባገነኑ የመለስ ቡድን በሚቀጥለው ሁለት ዓመት “የፓርላማ ምርጫውን አሸንፎ” ሥልጣኑን መቀጠሉ የማይቀር ነው። እንደተለመደው አገልጋይ ፓርቲዎችም ቁምነገር የሌለው ጥያቄ እያቀረቡ፣ የመለስ ቡድንም ለዴሞክራሲ ሽፋን ስለሚፈልጋቸው የተወሰነ መቀመጫ እየቸራቸው አብረው ይጓዛሉ። ካሁኑ መፍትሔ ካልተፈለገ የህወሓት/ኢህአዴግ ካድሬዎችና የአገልጋይ ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው ፓርላማም እንደ ተለመደው አቶ መለስ የራስ ወዳድነት ስሜቱን ለማርካትና “ሊቀ ሊቃውንት” እንዲባል ብቻውን እንደ አስተማሪ “ትምህርት” የሚሰጥበት፣ ሲያሰኘውም አገልጋዮቹ ተቃዋሚ

ፓርቲዎችን የሚዘልፍበት፣ ዴሞክራሲ እያበበ ነው ብሎ የሚሰብክበት፣ በድህነት ለሚሰቃየው ህዝብ ኢኮኖሚው አድጓል እያለ የሚለፍፍበት አሳዛኝ መድረክ ሆኖ ይቀጥላል። ካሁኑ መፍትሔ ካልተበጀለት የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣኖችና ተከታዮቻቸው የአገር ሀብት በግልፅ እየዘረፉ የሚኖሩበት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ስቃይና መከራ ግን እየተባባሰ መሄዱ የማይቀር ይሆናል። ካሁኑ መፍትሔ ካልተገኘ በኢትዮጵያ ባሊስትራ ብቻ ሳይሆን ከሱ ያነሰ ሌላ ንጥረነገርም ወርቅ የሚሆንበት ስለሆነም የአገር ክብርና ገፅታ በዓለም እየተበላሸ መሄዱ የማይቀር ይሆናል። ካሁኑ መፍትሔ ካልተገኘ የአገር አንድነትም እየላላ መሄዱ የማይቀር ይሆናል።

መፍትሔው የአገሪቱ ምሁርና የፖለቲካ ሊሂቅ ከስህተቱና ከውድቀቱ ተምሮ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በቁርጠኝነት መነሳት ነው። መፍትሔው የፓርቲና የግለሰብን የሥልጣን ጥቅም የማያስቀድሙ፣ ለዴሞክራሲ ግንባታ የሚታገሉ ሀቀኛ የዴሞክራሲያውያን ኃይሎች ህብረት መፍጠር ነው። መፍትሔው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚሳካው አገዛዙ በሚያደርገው "ምርጫ" ሳይሆን፣ ይህንን አምባገነናዊ ከሃዲ ቡድን በህዝብ ትግል ለማስወገድ በቆረጡ ለዚህም የተቀደሰ አገራዊ ዓላማ አስፈላጊውን ትብብር፣ ታክቲክና ስትራተጂ ነድፈው በሚታገሉ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ብቻ ይሆናል።

80 ሚሊዮን ህዝብ በአንድ አረመኒያዊ ኃይል ተረግጦ ሲገዛ፣ ያለመደራጀት ምን ያህል እንደሚያስጠቃ በከፋ ሁኔታ እየታየ ነው። ይህም ህዝባዊ ትግል ከመጠናከሩ በፊት ህዝቡ ራሱን ላደጋ በማያጋልጥበት መልክ መደራጀት እንደሚያስፈልገው ያስገነዝባል። ያገራችን አንድነትን ለመጠበቅና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በሚፈልጉ ኃይሎች ውስጥ በሥልጣን ሽኩቻ፣ በስግብግብነትና በጥቃቅን ልዩነቶች መለያየትና መናቆር ህዝባችን ያለበት አደጋ የማያገናዝብ ስለሆነ የተጠቀሱት ኃይሎች የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በህዝባዊ ትግል ዴሞክራሲና አንድነት በኢትዮጵያ እውን ይሆናል!!!
በተባበረ ህዝባዊ አመጽ አምባገነንነት ይወገዳል!!!
ኅብረት የህዝባዊ ትግል ጥንካሬ አብሳሪ ነው!!!

ከዓለም አቀፍ የትግራይ ተወላጆች ዴሞክራሲያዊ ማኅበር

ሚያዝያ 2008 ዓ.ም.ፈ.